# አሰፋ ጫቦ: "ፀረ-አብዮተኞች ታስረው እየተቀለቡ ስለሆነ ይገደሉ!" ብሎ ማመልከቻ አቅራቢው

ከመላኩ ይስማው

አቶ አሰፋ ጫቦ በኢሣት ላይ በ3 ተከታታይ ክፍሎች የሰጡትን ቃለ-መጠይቅ አዳምጫለሁ። በወያኔ ቁጥጥር ሥር በሚታተም አንድ ጋዜጣም ላይ የፃፉትን አንብቤያለሁ። (አንቱ የሚለውን ቅጽል በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀምኩት ለሰውዬው ሰብዕና ሳይሆን ለዕድሜያቸው አክብሮት ኖሮኝ በሀገራችን ባህል መሰረት መሆኑን ለአንባቢያን አስታውሳለሁ። ድንጋይም ይሸብታል እንዳትሉኝ እየጠየቅሁ።)

ህሊና የሚባል ዬት ሄደ? እውነትም ህሊና ቢስ ሰው ለመናገር አፉን በከፈተ ቁጥር፣ በላንቃው አልፎ የሚያሳየው የውስጥ ባዶነቱን ነው አሰኝተውኛል፤ ቃለ-መጠይቃቸውንም፣ ጽሁፋቸውንም ከጨረስኩ በኋላ።

እራሳቸው በቃለመጥይቁ ላይ እንደገለፁት - ወደ 7ኛ ክፍል እና 12ኛ ክፍል በውሸት የትምህርት ማስረጃዎች የገቡት አቶ አሰፋ ጫቦ ዛሬም ያው ናቸው። በውሸት ያደጉት፣ ከደርግ አንስቶ እስከ ወያኔ በውሸት ፖለቲከኛነት እጃቻቸውን በደም የታጠቡት አሰፋ ጫቦ አሁንም እነኛን የገደሏቸውን፣ የገረፏቸውን ሰማዕታት ታሪክ ሊገድሉ፣ እጃቸውን ሊታጠቡ ሲሞክሩ ታዘብኩና ይህን እንዲፅፍ አነሳሱኝ።

እስካሁንም እያታገሉን ያሉ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለምሳሌ መሬት ላራሹ፣ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር፣ የብሄረሰቦች እኩልነት ይከበር፣ ወዘተ በማንሳት ቀደም ሲል የንጉሱን፣ ኋላም የወታደራዊውን አገዛዝ ደርግን የተፋለመውን በአጠቃላይ ያን ትውልድ፣ በተናጠልም የኢሕአፓን አባላት በውሸት ክሳቸው ለመወንጀል ሞክረዋል። በተስፋዬ ደበሳይ ይጀምሩና። የደርግ ነፍሰ-ገዳይ ባንዳዎች እጄን አልሰጥም ብሎ እራሱን የሰዋውን የኢሕአፓ አመራር አባል ተስፋዬ ደበሳይን በመወንጀል። የተስፋዬን ኢትዮጵያዊነት ለመጠራጠራቸው መጠየቂያ ያደረጉትም - አዲስ አበባን አያውቅም፣ የኢሕአፓ አመራር ተደርጎ የተመረጠውም በሌለበት ነው የሚሉትን ነው። የመጀመሪያው - ተስፋዬ ደበሳይ አዲስ አበባን አያውቅም የሚለው - ከሃቅ ጋር የሚጣረዝ ነው፤ የሚያስቅም ጭምር። አቶ አሰፋ ለመሆኑ ተስፋዬ አባ ዲና ፖሊስ ያስተምር የነበረው ምን የሚባል ከተማ ኖሮ ነበር? ውሸት እና ቅራሬን ዓይንን ጨፍኖ ጭልጥ ነው እንዲሉ ልምድ ሆኖባቸው ይመስለኛል- እራሳቸው እንደተናገሩት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናቸውን በተጭበረበረ ማስረጃ የተቀበሉት፣ የዛሬው ሽበቶ አሰፋ ይህንን አላስፈላጊ ውሸት የተናገሩት። ወደ ዋናው ጥያቄ ስመጣ ግን - ለመሆኑ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማወቅ አዲስ አበባን ማወቅ የግድ የሚሆነው በምን ተጠየቅ ነው? እንኳን ከስንትና ስንት ዓመት በፊት፣ ዛሬም 85% በላዩ ህዝብ በግብርና ሥራ በገጠር በሚኖርባት ኢትዮጵያ፣ ከተሞቿን ያውም አንዱን አዲስ አበባን ማወቅ ብቸኛ የመለኪያ መስፈሪያ የሚሆነው በምን ስሌት ነው? ሀቅነት የለውም እንጂ ቢሆን ኖሮ፣ በሁኔታዎች አስገዳጅነት አንድ ሰው በስብሰባ ላይ መገኘት ሳይችል ቀርቶ ለአመራር አባልነት ሲመረጥ በግለሰብ ተስፋዬ፣ በድርጅት ኢሕአፓ ብቸኞቹ ናቸው ወይ? አያ ጂቦ ሳታመካኝ ብላኝ ካልሆነ በስተቀር። ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የኢሕአፓ አመራር አባል ተደርጎ የተመረጠው ደግሞ አቶ አሰፋ እንዳሉት በሌለበት አይደለም። ወደ አዲስ አበባ ሄዶ፣ ሀገር ቤት ከነበሩት ከነጸጋዬ ገብረመድኅን (ደብተራው) እና ሌሎችም ሀሳቡን ከሚደግፉት የተማሪው እንቅሥቃሴ መሪዎች ጋር ተመካክሮ፣ በመስራች ጉባዔውም ላይ መልዕክታቸውን ይዞ ተገኝቶ ነው።

ሌሎቹንም ታላላቆቹን ሕዝባዊ አርበኞች - ደብተራውን እና ሣሙኤልን - አንስተዋል። ሁለቱም ደርግንም ወያኔንም እስከ መጨረሻው እየተፋለሙ መላ ሕይወታቸውን የሰጡ ሕዝባዊ ሰማዕታት ናቸው። ክሶቹ የአቶ አሰፋና የመሰሎቻቸው የለመደ ፍብረካ ስለሆኑ አልገረመኝም። ግን አሁንስ ህሊና ዬት ሄደ? ለመሆኑ የንጉሱ

ጊዜ የጋርዱላ አውራጃ ገዢ የነበሩት፣ ከነፍሰ-ገዳዩ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ከፀረ-ኢትዮጵያው መለሰ ዜናዊ፣ የሀገራችንና የሕዝቧ መከራ የነፍስ አባት ከሆነችው አሜሪካ አምባሳደር ጋር ቤተኛ የሆኑ ሆዳም አድር ባይ አቶ አሰፋ በምን የህሊናና የሞራል መለኪያ ነው እነ ተስፋዬን፣ እነ ደብተራውን፣ እነ ሣሙኤል እና ሌሎችንም የሕዝብ ልጆች፣ ያን ትውልድ ለመክሰስ የሞራል ብቃት የሚኖራቸው?

በቃለ-መጠይቁ መግቢያ ላይ የኢሣቱ ሲሳይ "ለረጅም ዓመታት ከሕዝብ ዕይታ ለምን ተሰውረው ቆዩ?" በማለት ላቀረበላቸው ጥያቄ፤ ወያኔ እና ተቃዋሚዎቹ የሚያራምዱት አቋም በጣም የተፃረረ በመሆኑ፣ ሀቁ እስከሚገለጽላቸው ሱባዔ ገብተው እንደነበር መልሰዋል። ምነው አቶ አሰፋ!? በ1983 ዓ. ም. ወያኔ አዲስ አበባ እንደገባ ባዘጋጀው የአሻንጉሊቶቹ ስብሰባ ላይ ተሳትፈው ሀገር የመገነጣጠልንና ባህር በር የለሽ የማድረግን ውሳኔ ካስተላለፉ፣ ህዝብ የመለያያ ጊዜ ጠበቅ ቦንብ (ታይም ቦንብ) የተቀበረበት (አንቀጽ 39) እና የሀገር ድንበር ከዬት እስከ ዬት እንደሆነም የማይገልጽ ህገ-መንግሥት ያረገዘ የወያኔ የመደላደያ አልጋ ካደላደሉም በኋላ አገዛዙ ከተቃዋሚዎች ጋር ያለው ልዩነት አልገባዎት አለ? ወይስ እንደለመደበዎ እና ደርግን መቃወም ትክክል አልነበረም እንደሚሉት፣ አሁንም ወያኔን መቃወምም ትክክል አይደለም ለማለት ፈልገው ነው? ለማንኛውም ከሕዝብ ዕይታ ተሰውረው የነበረው ካመታት በፊት አንድ ከርሰዎ ጋራ ብዙ ወገኖችን የጨፈጨፈ ውስጥ አወቅ ሰው በደርግ ጊዜ ስለፈጸሙት ወንጀል ካናዳ ውስጥ በሚታተመው "ሐዋርያ" ጋዜጣ ላይ በሰፊው ጽፎብዎት ሰለነበረ ነው።

አሰፋ ጫቦ ከገዳዩ ደርግ ጋር በካድሬነት የማደራቸውን ተገቢነት ለማሳመን የሰጡት ምክንያት "የመሬት ላራሹ አዋጅ" ስለታወጀ ሌሎች ጉዳዩች ሁለተኛ ጥያቄዎች ናቸው የሚል ነው። በቅድሚያ ያገለገሏቸው ሁለቱም አገዛዞች - ደርግም ወያኔም - መሬት ለአራሹ ሳይሆን መሬት ለመንግሥት ነው ያደረጉት። ዳዊት የሚባሉ ገጣሚ፡

ሕዝብ በቀድሞ ዘመን፣ እንዲህ ግፍ ሲውሉበት፣

ቦምብ ይቀብር ነበር፣ በጠላቱ መሬት፣

ይህ ምሬት የገባው፣ ብልሁ መንግሥት፣

ሕዝብ እያመፀበት፣ ቦምብ ሲጠምድበት፣

መሬቱን ቀምቶ፣ ቦምብ ሆኖ መጣበት።




በሚሉት ስንኞች እንዳስቀመጡት አዋጁ ገበሬውን የግለሰብ ጭሰኛ ከመሆን የአገዛዞቹ ጭሰኛ ነው ያደረገው። እናም ያን ጊዜ ደርግና እናንተ አገልጋይ ካድሬዎቹ የጨፈጨፋችኋቸው የሕዝብ ልጆች በአጠቃላይ፣ የኢሕአፓ አባላት በተናጠልም የታገሉት "መሬት ለአራሹ ይሁን፣ ይህንንም የሚያረጋግጥ የሕዝብ ውክልና ያለው መንግሥት ለማምጣት የሚያስችል "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ይመስረት ብለው ነበር፣ አሁንም ነው። ፎቶ ከሺህ ቃላት በላይ የናገራል እንዲሉ ነውና

እርሰዎ ሀቅን በመሸፋፈን ሊከሱት የሞከሩት ያ ትውልድ የንጉሱንም የወታደሩንም አገዛዞች የተቃወመው ከላይ በተቀመጠው ምስል ላይ የተፃፉትንና መሰል መፈክሮች በማንገብ ነበር፡

አዎ!  ዋለልኝ የፃፈውን በመጥቀስ፣ ያ ትንታግ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ቀደም ሲል ከንጉሱ፣ ኋላም ከደርግ ጋር ያደረገውን ትግል ለመኮነን ሞክረዋል።  ለመሆኑ በዘር ላይ የተመሰረቱ ተጨቁነናል የሚሉ እንቅስቃሴዎች በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በሚካሄዱበት፣ በዚያን ወቅት ጉዳዩን ለመወያየት በተማሪው መካከል መነሳቱ ምንድነው ጥፋቱ?  ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት ላይ ያልነበረ ጉዳይ ከሆነስ፣ እንዴት ነው የዋለልኝ አንዲት ጽሑፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆና፣ ከ40 ዓመት በላይ ካለፈ በኋላ፣ ዛሬም ኢትዮጵያዊያንን የሚያወያይ፣ የሚያምሰን የሆነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያን ጊዜ ዛሬ ተገንጥላ ሀገር የሆነችው የኤርትራም ሆነ የትግራይ አንዳንድ ተወላጆች የሚያደርጉትን የመገንጠል ማቀንቀን በምን መንገድ ነው ማስቀረት የሚችሉት።  ችግሩ ሰለነበር ጥያቄው ተነሳ። የታሪክ ድርሳናት እንደሚመሰክሩት የንጉሱ መንግስት የኤርትራን መገንጠል አቀንቃኞች ለመቋቋም በማሰብም ይሁን ''እሾህን በሾህ ነው'' የሚለውን ብሂል ተከትሎ ጀበሃን ለማክሸፍ በማለም፤ ያን ጊዜ የጠቅላይ ግዛቱ ሹም በነበሩት በልዑል አሥራተ ካሣ እና በአሜሪካዎች ምክክር ዛሬ ገንጥሎ ገዢ የሆነውን ሻዕቢያን አቋቋሙ። በሀገር አንድነት የሚያምኑ ለውጥ አራማጅ ኢትዮጵያዊያን (የኤርትራ እና  የትግራይ ተወላጆች የሆኑም ጭምር) ደግሞ ኢሕአፓን መስረተው፣ የሀገር አንድነት የሚረጋገጥበት  ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለማምጣት ትግላቸውን ቀጠሉ።  ታሪኩ በአጭሩ ይኸ ነው፣ እርሰዎ ጭቃ ለመቀባት እንደሞከሩት ሳይሆን።  በዚያም በዚህም ብለው ያን ትውልድ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም አራማጅ አድርጎ ለማሳየት ነውና ዓላማዎ፣ አውሮፕላን ጠለፋዎችም ሆኑ ሌሎች በኢትዮጵያዊያን የተደረጉ እንቅስቃሴዎች በኤርትራ ተገንጣዮች የተዘወሩ እንደነበሩ ድፍን ያለ ክስ አቅርበዋል።   የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት እና የመገንጠል መብት እውቅና ካልሰጣችሁ ተብለው ኤርትራ ውስጥ ታግተው አንድ ዓመት የቆዩትንም የኢሕአፓ እርሾ ጦር አባላት፣ ከተገንጣዮቹ ጋር በማበር የኢትዮጵያን ጦር ሲወጉ እንደነበር፣ ኋላ ላይ ከድቶ የህዝብ ልጆች ገዳይ የሆነው ደርግ ሹም የሆነው ተስፋዬ መኮንን ምስክር በማድረግ ከሰዋል።  ሀቁ ግን ተገላቢጦሽ ነው።  ኢሕአፓ በአንድነት ላይ ትላንትም ዛሬም አልደራደርም በማለቱ  በሻዕቢያም ሆነ በሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ጥርስ እንደተነከሰበት እራሱ የጻፈውን ብቻ አይደለም፣ ከዚህ ቀደም መሳሪያ የተማዘዙት እነገብሩ አሥራት ሳይቀሩ እንደመሰከሩለት፣ የተጠቀሱት ግለሰብ በቅርቡ ያሳተሙትን መጽሐፍ ማንበብ ይበቃል።  በማይነቃነቀው የአንድነት መርሁ ጥላ ሥርም ኤርትራን፣ ትግራይንም ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያዊይዊን በሀገሪቱ አራቱም ማዕዘኖች ሕይወታቸውን ገብረዋል። ተስፋዬ ደበሳይ፣ ጋይምን ጨምሮ።

የንጉሱ አገዛዝ መውደቁንም ተከትሎ፣ በአጭሩ ደርግ ከተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች የሚወከሉ ለሚያቋቁሙት የሲቪል መንግሥት ስልጣኑን ያስረክብ ነው የዚያ ትውልድ፣ የኢሕአፓ አባላት ያሉት።  እርሰዎና መሰሎችዎ ደግሞ በተቃራኒው በመቆም በመላው ኢትዮጵያ ጨፈጨፉችኋቸው።  ጋሞጎፋ ውስጥ የደርጉ የሕዝብ ድርጅት ፀሐፊ በነበሩ ጊዜ የኢንዱስትሪያል አርት አስተማሪውን ተሾመን፣ ትንሽ ቡና ቤት የነበረውን ተፈሪን፣ በንጉሡ ጊዜ ባለሥልጣን የነበሩትን የሰለሞንን/የገነትን አባት፣ ካሳ ኮታንና አባቱን ፊታውራሪ ኮታ ከምቦን፣ ሌሎችንም አርባ ምንጭ ውስጥ፣ በመሎ ተስፋዬ እንግዳ እና አባቱን እንግዳ መንገሻን፣ ተስፋዬ ታፈሰን እና አባቱን ታፈሰ ገብረሕይወትን፣ እና ሌሎችንም ለምን  አስገደሏቸው?  በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ዘር፣ ሃይማኖት ሳይለያቸው በኢሕአፓ ጥላ ሥር ይደረግ የነበረው ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ የመጤዎች ትግል ነው በማለት፣ ለምን ነበር በሀሰት ይቀሰቅሱ የነበረው?  ይህንንም መስመር በማቀንቀን በየቦታው መጤ፣ ነፍጠኛ ናቸው በማለት ብዙ ንጹሀንን በካድሬዎችዎ አስጨርሰዋል።  ምሳሌ ልጥቀስልህ እችላለሁ፡  ድሜ ገርፋ እና መስኪቶ የሚባለው አካባቢ በግብርና ይተዳደሩ ከነበሩ ውስጥ አቶ ገረመውና ወንድማቸውን ጨምሮ ከ20 በላይ ሰዎች ፣ ጊዶሌ - ጉማይደ ተብሎ በሚጠራውም ስፍራ ቁጥራቸው የበዛ ኗሪዎች መጤና አድሃሪ ተብለው ተገድለዋል፣ ተባረዋል።  በመስኪቶ ከተገደሉት ሰዎችም ውስጥ የአካባቢው ተወላጅ የነበሩት አቶ አድማሱ ገርዳ የሚጠቀሱ ናቸው።   የእርሳቸው ወንጀል ያላችሁትም በነበራቸው ተራማጅ (ፕሮግሬሲቭ) አመለካከት ሕዝቡ

የሚወዳቸውና አብሮ መኖርን የሚሰብኩ መሆናቸው ነበር። አርቆ አሳቢ የሆኑ እንደሳቸው ዓይነት ሰዎች የጣሉት የአብሮነት እርሾም ይኸው እስከዛሬም የታሪካችን ቅርስ ሆኖ፣ በዘመነ ወያኔም ጊዜ ጋሞጎፋ ውስጥ ከሁሉ አስቀድሞ የትምህርት ቋንቋችን የሀገራችን የጋራ መግባቢያ የሆነው አማርኛ ይሁንልን ያለው ያ አካባቢ ነው። በጂንካም አስር አለቃ አሰፋና ሌሎችንም ተገድለዋል። እርሰዎ ግን የተጠቀሱትን አይነት ጭፍጨፋዎቻችሁን፣ ለደርግ ሰኔ 4 ቀን 1969 ዓ. ም. በተፃፈ ደብዳቤ ሲዘግቡ እንዲህ ነበር ያሉት፡

የጋሙ ጎፋ ክፍለ ሀገር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በ
የካቲት 66 የፈነዳውን ዐብዮታዊ ትግል ለማፋፋም ከፍተኛ አስተዋ
ጽዖ አድርጓል:: ፀረ አብዮት አቋም ያላቸውን አናርኪስቶች፣ አድኃሪ ያገ
የመሬት ከበርቴዎችና የቢሮ ከበርቴዎችን በማጋለጥ አስፈላጊው አብዮ
ታዊ ቁጣ በመንግሥት በኩል እንዲወሰን አድርጓል:: ስለሆነም በበ

ከእናንተ ቡራኬ ውጭም የመረዳጃ ማኅበር ማቋቋምንም እንኳ ታወግዙ ነበር፡

በሌላም አንፃር ከወለበተኛው ፕሮግራም ጋር የሚደራጁ ክፍሎችን
ለመቆጣጠር አስፈላጊው ጥረት መደረግ ይኖርበታል:: ለምሳሌ በገለ
ብና ሰፈር ባሮ ~~አብዮሩኛ~~ የተደራጀው የጡረተኞች ማኅበር ከምን አን
ፃር እንደሆነ ለከበተላን አልቻለም:: በተለይም ከእነዚህ የጡረ
ታ ማኅበር አባሎች ውስጥ የመሬት ከበርቴዎች የነበሩና የከተማ
ቦታና ትርፍ ቤት ያስረከቡና በአወከር የተፈታ ስለሉ በማኅበር
የመደራጀታቸው ጉዳይ ለህብረቱ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል::
በተጨማሪም ወለበተኛው ፕሮግራም አቀፍ የሚይዘው ማኅበር አድርጎ
በመገመት ትጥቅ እንዲሰጣቸው ይደረጋል የሚል ዝንባሌ እንዳለ ጭ
ምጭምታ ሰምተናል::

በማስከተልም እስረኞችቻሁ ታስረው መቀለብ ስለሌባቸው ሊገደሉ ይገባል የሚል ውሳኔ ከካድሬዎችዎ ጋር ማስተላለፋችሁን፡

ለ/ በፀረ አብዮተኞች ላይ ማስረጃ ተገኝቶ በወህኒ ከተቆጠሩ በኋላ እስከሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለገደብ ጥቆምና ያለ ምክንያት የሚቀለቡ በክፍለ ሀገር ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። ይኸውም በቢሮክራሲያዊ ዳተኝነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ምናልባት ኢዲዩ ኢህአፓ በመጠናከር ሥልጣን ሊይዙ በደገኝነት ለማጎረበብ የተቆጠሩ፣ በሕልም ቅዠት የተጠከረ ባይሆኑ አይቀሬም፡ የሚል ግምት አለ። የአብዮትን ደረጃ ጥራትና የአብዮታዊያንን ሞራል ለመጠበቅ እንዲሁም ዳተኝነትን ለማስወገድ በፀረ አብዮተኝነት በወህኒ ቤት በሚገኙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን ጉባዔው አምኖበታል።

በማለት ገልፀዋል።


በግፍ የጨፈጨፉችኋቸውን ሰማዕታት ታሪክ የውሸት ጭቃ በመቀባት፣ ዳግም ሐቅን ለመግደል ከመሞከር ይልቅ፣ በዚህ የሸበት ዕድሜዎ እውነትን በመናገር ከራስዎ ህሊና ጋር መታረቅ ይሻል ነበር። መቼም ከኔ በላይ የሚል አጉል ነገር ተጠናውቶዎታልና ያንንም ይህንንም በማንሳት እዚያ እዚህ ሲረግጡ ከብዙ ሃቆች ጋር ተላትመዋል። ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ጀምሮ እስካሁንም አገልጋያቸው የሆነውን ተስፋዬ ሃቢሶን የተዋጣለት ሠራተኛ ብለው ሲክቡ ፊታውራሪ መኮንን ዶሪን እና ዶ/ር በየነ ጴጥሮስን ከአገዛዙ ጋር የሚሞዳሞዱ ብለዋል። ሰዎቹ የራሳቸው መልስ እንደሚኖራቸው አምናለሁ። እንደ አንድ ተራ ኢትዮጵያዊ እስከማውቀው ግን፣ ቢያንስ ከወያኔ ጋር ሥልጣን ካልተጋሩ እና ከተገለሉ ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ጋር ጭምር ፓሪስ ውስጥ በተደረገው ምክክር የተመሰረተውን ህብረት እውቅና በመስጠታቸውና አባልነታቸውን በመቀጠላቸው ከአገዛዙ ጋር ተጣልተዋል። ፊታውራሪም ሰበብ ተፈብርኮባቸው ታስረዋል።

በመጨረሻም ሀገርን ከፋፍሎ፣ ወደማያባራ መተላለቅ ለመውሰድ ታልሞ በወያኔ ህገ-መንግሥት ተብዬው ውስጥ የተካተተውን አንቀጽ 39ን ለምን ደገፉ በማለት ሲሳይ ሲጠይቀዎት አለባብሰውና ያንኑ የፈረደብትን ዋለልኝ መኮንን በመክሰስ አልፈውታል። ከ40 ዓመት በፊት የተፃፈ ጽሑፍ ዛሬ ላደረጉት ዘረኛነትን የመደገፍ እርምጃ እንዴት ብሎ ሰበብ እንደሚሆን ግራ የሚያጋባ ነው። ውሸት እና በራ ሲያመልጥ አያስታውቅም እንዲሉ፤ በአንድ በኩል ህገ-መንግሥቱን ፈርሜ አላፀደቅሁም እያሉ፣ በሌላ በኩል ህገ-መንግሥቱን እኔ ነኝ ያዘጋጀሁት ይሉናል፤ እራሰዎን በአገዛዙ ተፈላጊ ለማድረግ። ታዲያ ይኸስ ለምን አያሰኝም? ይኸንኑ ከእኔ በላይ ጉራዎትን ለማሳየት በማሰብ ይመስላል፣ በደርግ እስር ቤት እያሉም አገዛዙ ምክርዎትን በጽሑፍ እንዲሰጡት ያደርግ እንደነበረ እና መርማሪውን "ወግድ ወዲያ!" ብለው እንዳባረሩት ይፎገላሉ - በዚሁ ጉደኛ ቃለ-መጠቅ ውስጥ። እርስዎ ልዩ እንክብካቤ የሚደረግለዎ ልዩ እስረኛ ነበሩ ወይስ እንኳንስ ተናግረው ታስባላችሁ ብለው የሚገሉትን የደርግ ነፍሰ-ገዳዮች በፍርሃት የሚያንጳረጵር ልዩ ያፍዝ ያደንግዝ ነበረዎት?

ለወያኔ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ይቅርታ ለማስገኘት እና አሁንም ቢያስጠጉኝ ብለው እንደሚመኙ በሚያሳብቅበዎት ሁኔታም - በአጭሩ ሲጠቃለል - የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ያስከተለውን የትግሬዎችን ማይንድ ሴት አውቃለሁ፣ ከሚያወሩኝ የተገነዘብኩት በዘመነ-መሣፍንት አጥር ውስጥ እንዳሉ ነው። ተቃዋሚው እንደሚላቸው ድርጊታቸውን ፀረ-ኢትዮጵያ አድርገው አያዩትም፤ ተቃዋሚውም ይህንን አይገነዘብላቸውም፤

አቋማችሁን አንቀበልም እያለ መገናኛ አሳጥቷቸዋል። በ97 የነበረውን ትንሽ ቀዳዳም በማጥበብ የባሰ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው - በማለት መልሰዋል። መቼም ያው የለከፈዎት ለመጣው አገዛዝ የማደር አባዜ ዛሬም አለቀዎት ብሎ እንጂ እርስዎ የገቡበት ቀዳዳ ጠቦ እኮ በስደት ላይ ነው ያሉት። ደግሞስ የዴሞክራሲ እና የአብሮ መኖር (የአንድነት) ጥያቄን አሳልፎ ከሰጠ ተቃዋሚው ፄት መንገድ ላይ ነው አታግለዋለሁ ከሚለው ሕዝብ ጋር የሚገናኘው? ወይስ ትላንትና እርሰዎ እና መሰሎችዎ ከደርግ እና ከወያኔ ጋር በመሞዳሞድ የሕዝብ ጥያቄን ጭዳ እንዳደረጋችሁት ከህደት ይፈጽም የሚል ነው ምክረዎ? ለካስ አብዬ የድንጋይ ሽበት የሚሉት ወደው አይደለም! ደግሞም ሌላ ጊዜ በቃለ-መጠይቅ በተለይም በቴሌብዥን ላይ ሲቀርቡ፣ አሁን ከሲሳይ ጋር ሲነጋገሩ እንዳደረጉት፣ ከፔርሙዝ መሳዩ ዕቃ ንጥረ-ነገር ከመጎንጨት ቢታቀቡ ጥሩ ነው። አልኮል ውል ያስታልና።

ለማንኛውም አንባቢያኔም፣ እርስዎም [ከዚህ ላይ በመጠቆም](#) ከዛሬ 38 ዓመት በፊት ከአባሪ ካድሬዎችዎ ጋር ሆናችሁ፣ የሕዝብ ልጆች ላይ ስላካሄዳችሁት ጭፍጨፋና አፈና ለነፍሰ-ገዳዩ ደርግ የላካችሁትን ዘገባ እንዲያነቡ እጋብዛለሁ። አሌ እንዳይሉ ደግሞ ዘገባውን የራስዎ ፊርማ ካረፈበት ሽኝ ደብዳቤ ጋር እንዲህ በማለት ነበር የላኩት፡




[(ሙሉውን ደብዳቤ እዚህ ተጭነው ያንብቡ)](#)